

DISCOVER
ITS BEAUTY

ክፍል 4

# የሰብአዊነት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ

ዶ/ር ናጂ ኢብራሂም



# የሰብአዊነት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ

እስልምና የሰው ልጅን ወሳኝ ጥያቄዎች በግልፅ ይመልሳል፡-

- እውነታው ምንድን ነው?
- ማን ፈጠረን?
- አምላክ አለ?
- እውነተኛ አምላካችን ማነው?
- የመጨረሻው የአላህ ነብይ ማን ነው?
- ማንን ማምለክ አለብን?
- እኛ ማን ነን?
- እዚህ ያለንበት ምክንያት ለምንድን ነው?
- እንሞታለን ወይስ አንሞትም?
- ከሞትን በኋላ ምንድነው የሚፈጠረው?
- ቀጣዩ ህይወት (ኣኺራ) ምን ይመስላል?
- የመጨረሻው መዳረሻችን የት ነው የሚሆነው - ጀነት ወይስ ጀሀነም?
- እውነተኛ የአእምሮ ሰላም፣ ስኬት እና እውነተኛ ደስታ ማግኘት የምን ችለው እንዴት ነው?
- የዘላለም ሕይወት ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?

**አእምሮአችሁን እና ልባችሁን እውነትን በመፈለግ ላይ አድር ጋችሁ፣ እባካችሁን በታማኝነት አንብቡ እና ለራሳችሁ ፍረዱ።**

# እውነታ

# እውነት ምንድን ነው?

እስልምና አንድ አምላክ (አላህ) ፍጥረታትን በሙሉ እንደፈጠረ ይነግረናል። ሰዎችን እና እንስሳትን፤ ምድርን እና ተራራዎችን፣ ውቅያኖሶችን እና ወንዞችን፣ ተክሎችን እና ደኖችን፤ ፀሐይን እና ጨረቃን፣ ጋላክሲዎችን እና ምህዋሮችን፤ እና ቀንን እና ለሊትን ሁሉ የፈጠረው ይህ ታላቅ አምላክ ብቻ ነው። እኛ የምናውቃቸውን እና ገና ያልተገኙን ጨምሮ ሁሉም ሌሎች ነገሮች የእርሱ ገደብ የለሽ የፍጥረት ገጽታዎች ናቸው።

በምድር ላይ ያለውን ህይወት ሁሉ የፈጠረው አላህ ሲሆን መላውን አጽናፈ ሰማይን በጊዜ፣ በቦታ፣ በሐይል እና በቁስ ፈጥሯል። አላህ አጽናፈ ሰማይን እና በውስጡ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ይደግፋል እና በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ የሚከሰተውን ሁሉ ይቆጣጠራል።

ሆኖም፣ አንዳንድ ሰዎች ሕልውናቸውን **'በአጋጣሚ'** ወይም **'በተፈጥሮ'** ነው ይላሉ! በሳይንሳዊ አነጋገር ተፈጥሮ ምን ማለታቸው እንደሆነ እንግለፅ! **'ተፈጥሮ'** ምንድን ነው?

ተፈጥሮ ማለት፤ ፕላኔቶች፣ ምህዋሮች እና ጋላክሲዎች፤ ሸለቆዎች እና ተራሮች፣ ውቅያኖሶች እና ወንዞች፤ ምድር፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት እና ሌሎች ነገሮች እንደሆኑ እንስማማለን አይደል? ታዲያ እነዚህ ነገሮች እራሳቸውን ፈጥረዋል? የሰው ልጆችን ፈጥረዋልን?

የተከበረው ቁርኣን በሚያምር ሁኔታ እንዲህ ይለናል፡-

**እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።** (2:21)

**ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ።** (39:5)

**እርሱም ሌሊትንና ቀንን፣ ፀሐይንና ጨረቃንም የፈጠረ ነው።** (21:33)

# አላህ

## እውነተኛው
## አምላክ ነው

ብዙውን ጊዜ፣ በተፈጥሮ ብቻ የሚያምኑ ሰዎች እሱን ማየት፣ መንካት ወይም ሙከራ ስላላደረጉ ብቻ በፈጣሪ አናምንም ብለው ይከራከራሉ!

ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ በኦሪገን፣ አሜሪካ፣ አንድ አረጋዊ ጎረቤቴ ቤት መጥተው ጠየቁኝ። ስለ ብዙ ነገሮች ተነጋገርን፣ ከነዚህም ውስጥ አንዱ ስለ አላህ (ፈጣሪ) ጽንሰ-ሐሳብ ነበር። የፈጣሪን መኖር በመካድ የሻይ ጠረጴዛ ውን አንኳኳ፣ በስሜት "መንካት ስለምችል!... ስለሚሰማኝ! በዚህ ጠረጴዛ አምናለሁ" እሱ ካነሳው ነጥብ ላይ ተነስቼ፣ በክፍሉ ውስጥ ወዳለው መብራት ጠቆምኩና "በኤሌክትሪክ ታምናለህ?" እርሱም፡- “አዎን” ሲል መለሰ። "መብራቱን የሚያመነጨውን ኃይል ወይም ጉልበት ማየት ትች ላለህ?" ብዬ ጠየኩት "አይ" ሲል መለሰ። እኔም ‘የምንተነፍሰውን አየር በራስህ አይን አይተህ ታውቃለህ? ሐሳቡ ራሱ አለህ? ቀለሞቻቸው፣ ቅር ጻቸው እና መጠኖቻቸው እንዴት ሊሆን እንደሚችል? እንቅልፍ ምንድን ነው? ቀለሙ ወይም ክብደቱ ምን ያህል ነው? በትክክል ሳናያቸው ስንት ነገር እናምናለን?

በሌላ አጋጣሚ ክሪስ የሚባል አንድ ወጣት እና ባለቤቱ በኦስሎ፣ ኖርዌይ በሚገኝ ሆቴል ውስጥ አገኘኋቸው። ከእነሱ ጋር ወዳጃዊ በሆነ ውይይት ላይ ክሪስን "የህይወት አላማ ምንድን ነው?" በመገረም "እንደዚህ አይት ጥያቄ ስሰማ የመጀመሪያ ነው!" አክሎም “ለሕይወቴ ምንም ዓላማ እንደሌለ አስ ባለሁ” እና “በማንኛውም አምላክ አላምንም” ሲል ደመደመ። ለምን እንደ ሆነ ጠየኩት እና "እስካሁን አላየሁትም" ሲል ገለጸልኝ። በመልሱ ላይ አስተ ያየት ስሰጥ (በፈገግታ) "ሚስትህን ትወዳለህን? ይህን ፍቅር በአካል ማየት ትችላለህ? የፍቅርህ ቀለም ምንድነው? ይህ ፍቅር ምን ያህል ክብደት አለው?" ክሪስ እና ሚስቱ ምን ምላሽ ሰጡ? በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል ሞክር!



ይህንን ረቂቅ ፍቅር ማየትም ሆነ መለካት አለመቻል እውነትንና ህልውና ውን ወደ መካድ እንደማይመራው ግልጽ ነው።

በተመሳሳይ አመክንዮ፣ ፈጣሪን መመልከት ስለማንችል ብቻ (ታላቅነቱን ሊረዱት በማይችሉት በእኛ ውስን ችሎታዎች እና ስሜቶች)፣ ይህ ህልውና ውን እንድንክድ ሊያደርገን አይገባም።

ስፍር ቁጥር በሌላቸው አተሞች፣ ህዋሶች፣ ሕብረ-ህዋሶች እና ጡንቻዎች አፈጣጠር እና በሁሉም ሰው እና በፈጠረው ነገር ሁሉ በተገለጠው ገደብ የለሽ ምልክቶች እና ማረጋገጫዎች ውስጥ የአላህ ህልውና በግልጽ እና በቀላሉ ሊገኝ የሚችል ነው።

በሺዎች የሚቆጠሩ የአላህ ነቢያት (ስማቸውን የምናውቃቸው የተወሰኑ ትን ብቻ ነው) እንዲሁም በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በነበሩት በቢሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮቻቸው የአላህን መኖር አረጋግጠዋል። በእውነቱ ሳይን ሳዊ ንድፈ ሐሳቦች አጽናፈ ሰማይን ብቻ ሲገልጹ እና ይህን አጽናፈ ሰማይ ምን ወይም ማን እንደፈጠረው እና እንደዚያ እንዳደረገው ሳይጠይቁ ለ'ሳ ይንስ' ብቻ በመደገፍ የእነዚህን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች እና ምልክቶ ችን ችላ ማለት ምክንያታዊ ነው? እንደውም ሳይንሳዊ መረጃዎች እንደሚ ያመለክቱት የአጽናፈ ዓለማችን 'በአጋጣሚ' የመፈጠር ዕድሎች በእውነቱ በአእምሮ ለመገንዘብ በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም 'አጋጣሚ' ግን ኢ-አማኒ ያን ለጽንፈ ዓለማት ሕልውና እና ለተፈጥሮ የሚያቀርቡት ብቸኛው ማብ ራሪያ ነው፤ በነሱ ሀሳብ፣ **'እንዲሁ ነው የሆነው'**።

ከዚህ አንፃር፣ እባካችሁ የትኛው እምነት ይበልጥ ምክንያታዊ እንደሆነ አስቡ ዕውር ዕድል ሁሉንም የሚገዛ ነው ወይንስ አጽናፈ ሰማይ የተፈጠረ እና የሚቆጣጠረው በአላህ (አምላክ) ስለሆነ ነው?



# እነዚህን ጥያቄዎች ያስቡባቸው

- **አጽናፈ ዓለም የማሰብ ችሎታ ባለው ፈጣሪ ነው ወይስ በድፍኑ በአጋ ጣሚ የተገኘ ነው?**
- **‘ሳይንስ’ ወይም ‘የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብ’ የአምላክን መኖር ያስ ተባብላል?**

በእስልምና ውስጥ ያለው እውነት ቀላል ነው። የዓለማት ፈጣሪ እና ጠባቂ አንድ አምላክ ብቻ አለ (የተባረከና ከፍ ያለ ነው)። ማንንም ወይም ማንኛው ንም ነገር ከእሱ በላይ ወይም እኩል አድርገን መቁጠር የለብንም። አንድ እውነ ተኛ አምላክ አላህ እሱን ብቻ እንድናውቀው እና እንድናመልከው አድርጎ ፈጥ ሮናል።

እርሱን በትክክል የሚያመልኩ ትእዛዛቱን ሙሉ በሙሉ በመከተል በጀነት ውስጥ ዘላለማዊ ህይወትን ይኖራሉ።

በሌላ በኩል አላህን የማይታዘዙ፣ ኃጢአተኛ ምኞታቸውንና ፍላጎታቸውን በመ ከተል፣ ሌሎችን እየበዘበዙና እየጨቆኑ ወደ... ይወሰዳሉ፣ የት ጠብቃችሁ ነው?

እውነተኛ ደስታ እና የአእምሮ ሰላም ማግኘት የምንችለው አንድ አምላክ ለሆነው አላህ በማመን እና በመገዛት ብቻ ነው።




الله أكبر
አላህ ታላቅ ነው

# እውነተኛው አምላክ ማን ነው?

እስልምና ይህንን ወሳኝ ጥያቄ በግልፅ እና በሚያምር ሁኔታ ይመልሳል እና ስለ አንድ እውነተኛ አምላክ ልዩ ተፈጥሮ እና ባህሪያት በዝርዝር ገልጿል። የተከበረው ቁርኣን እንዲህ ይላል።

**በል «እርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። አልወለደም፤ አልተወለደምም። ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።»** (112: 1-4)

ከላይ ያለው የተከበረው የቁርኣን ሙሉ ምዕራፍ ነው። ይህ አስደናቂ ምዕራፍ ባጭሩ ስለ አንድ እውነተኛ አምላክ ስለ አላህ እና ስለ እሱ እውነተኛ ተፈጥሮው የመጨረሻውን እውነት ያስተላልፋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ግራ የሚያጋቡ አስፈላጊ ጥያቄዎችን በግልፅ ይመልሳል።

አምላክ ነን ከሚሉ (ወይም ከሚባሉት) ፍጥረታት መካከል እውነተኛውን አምላክ አላህን ከሚለዩት ባህሪያት ጥቂቶቹ፡-

- ይህ እውነተኛ አምላክ ፈጣሪ ነው አልተፈጠረም አልተወለደምም።
- ይህ እውነተኛ አምላክ አንድ ብቻ ነው። አጋሮች ወይም አቻዎች የሉትም።
- ይህ እውነተኛ አምላክ በዚህ ሕይወት ለእኛ የማይታይ ነው።
- ይህ አንድ እውነተኛ አምላክ በፍጡራኑውስጥ በየትኛውም መልኩ በአካል አልተገለጠም።
- ይህ እውነተኛ አምላክ ዘላለማዊ ነው፤ አይሞትም አይለወጥም። እሱም ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር ይሆናል።
- ይህ አንድ እውነተኛ አምላክ እንደ እናት፣ ሚስት ወይም ወንድ ልጅ ምንም ወይም ማንንም አይፈልግም፤ ወይም ምግብ፣ መጠጥ፣ ወይም ምንም ዓይነት እርዳታ አይፈልግም። እሱን የሚፈልጉት ሌሎች ናቸው።
- ይህ አንድ እውነተኛ አምላክ በባህሪው ልዩ ነው። እርሱን የሚመስለው ማንም የለም፣ የሰውም ሆነ የእንስሳት ባህሪያት ለእርሱ ሊሆኑ አይችሉም።



# የአእምሮ ሰላም ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?

በእርግጥም እስልምና ተፈጥሮአችንን አውቆ ለጥያቄዎቻችን መልስ ይሰጣል። ለነፍሳችን እና ለመንፈሳዊ እና አእምሮአዊ ፍላጎቶቻችን እና ዝንባሌዎቻችን ይናገራል። በነፍሳችን፣ በአእምሯችን እና በልባችን ውስጥ ያሉትን ጥልቅ ሚስጥሮች እና ሀሳቦች የሚያውቀው አላህ እርጋታን እና እርካታን የሚያመጣባቸውን ሚስጥሮች ገልጦልናል።

የአእምሮ ሰላም እንድናገኝ የሚረዱን አንዳንድ ቁልፎች እና ምስጢሮች እነዚህ ናቸው፡-

1) እውነተኛ አምላካችሁን፣ ፈጣሪያችሁን ማወቅ።

2) በእርሱ ብቻ ማመን።

3) ፈቃዱን መከተል እና ለእሱ መታዘዝ።

4) በነቢያቱ (ነብዩ ሙሐመድን ጨምሮ) ማመን።

5) እሱን ማስታወስ።

6) ምህረቱን መፈለግ።

7) እርሱን በብቸኝነት ማምለክ።

8) ለራሳችሁ የምትመኙትን ለሌሎች መመኘት::

9) ለሌሎች ለጋስ መሆን እና እነሱን ለማስደሰት መሞከር።

10) ቅን እና ፈሪ መሆን።



# ማጠቃለያ

እነዚህ የአዕምሮ ሰላምን፣ መረጋጋትን እና እርካታን እንዲሁም መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ እና አለም አቀፋዊ ሰላምን የማግኘት ሚስጥሮች የክቡር ቁርኣን ድንቅ ሀብት እና የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አባባሎች ናቸው።

ለማጠቃለል ያህል እስልምና ለሰው ልጅ ወሳኝ እና አስፈላጊ ጥያቄዎችን ይመልሳል እና በሁለቱ ዋና ዋና የተረጋገጡ ምንጮቹ (በተከበረው ቁርኣን እና የነብዩ ሙሀመድ ንግግሮች) የአዕምሮ ሰላም፣ ደስታ እና መዳንን የምናገኘው በፈቃደኝነት እና በሙሉ ልብ ብቸኛ እና እውነተኛ የሆነውን አላህን በማወቅ እና በማመን ብቻ እንደሆነ ያስተምረናል። በሁሉም የአላህ እውነተኛ ነብያት (ነብዩ ሙሐመድን ጨምሮ) ማመን እና እውነተኛ መመሪያቸውን እና አስተምህሮታቸውን መከተል ይኖርብናል።



# በእስልምና ውስጥ የዋና ስሞች ፍቺዎች

**አላህ፡-** በአረብኛ "አላህ" የአንዱ እውነተኛ አምላክ፣ ፈጣሪ ትክክለኛ ስም ነው። እስልምና አላህ የሰው ልጆች ሁሉ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል። የአይሁድ እና የክርስቲያን አረቦች አምላክን ለማመ ልከት አላህ የሚለውን ስም ይጠቀማሉ፣ እና በአረብኛ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ነው።

**ሙሐመድ፡-** (የአላህ በረከትና ሰላም በእሱ ላይ ይሁን)፡- የአንዱ እው ነተኛ አምላክ፣ ፈጣሪ የሆነው የአላህ የመጨረሻ ነብይ፤ ለሰው ልጆች ሁሉ የተላከ።

**የተከበረው ቁርአን፡-** ለነቢዩ ሙሐመድ የወረደው አንድ እውነተኛ አምላክ የሆነው የአላህ የመጨረሻ ቃል።

**እስልምና፡-** አንድ እውነተኛ አምላክ ለሆነው ለአላህ ፈቃድ መገዛት ነው።

**ሙስሊም፡-** አንድ እውነተኛ አምላክ ለሆነው አላህ የተገዛ እና እርሱን ብቻ የሚያመልክ ነው።

**መስጂድ፡-** ሙስሊሞች በዋናነት ለሶላት እና ለአምልኮ የሚጠቀሙ በት ንፁህ የስግደት ቦታ ነው።



አላህ በአረብኛ



አላህን (እውነተኛውን አምላክ) የሚማፀን ሙስሊም



የተከበረው ቁርኣን



ሙሐመድ በአረብኛ

# የማወቅ ጉጉት አልዎት?

የማወቅ ጉጉት ካሎት እና ስለ እስልምና ተጨማሪ መረጃ እና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ እባክዎን ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ፡-

**www.discoveritsbeauty.com**

## የውበቱን ያግኙ ተከታታይ ቡክሌቶች፡-

1. ከብዙው በትንሹ
2. የአደም እና የሐዋ ሃይማኖት
3. የእስልምና መሠረቶች
4. የሰብአዊነት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ
5. የእርሱ መልካም ስሞች
6. የመጨረሻው ወህይ
7. የመጨረሻው መልእክተኛ

## ጠቃሚ ኢስላማዊ ድረ-ገጾች፡-

**http://www.allahsquran.com**

**http://www.quranexplorer.com**

**http://www.islamhouse.com**

**http://www.edialogue.org**

**http://www.islamreligion.com**

**http://www.newmuslimguide.com**

**http://www.guidetoislam.com/en/**

# የእምነት ምስክርነት (የእስልምና መግቢያ በር)

“ከአላህ በስተቀር በእውነት እና በብቸኝነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።”

በአረብኛ እንዲህ ይነበባል፦


أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللهُ وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ


ሲነበብ ይህን ይመስላል፦

**አሽ-ሀዱ አላ ኢላሀ ኢለ ሏህ**

**ወ አሽ-ሀዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ**

ይህ አንድ ሰው እስልምናን ለመቀበል በአፉ መናገር ያለበት የእምነት ምስክርነት ነው። የእስልምናን እውነተኛነት፣ ውበት እና ቀላልነት አንድ ላይ ይዟል።






GLOBAL ACADEMY FOR TRANSLATION AND EDUCATION (GATE)
LONDON | THE UNITED KINGDOM

በAL-ANDALUS GROUP LTD የተተረጎመ
www.alandalusgroup.org

كتاب الإجابة عن تساؤلات البشرية الحاسمة باللغة الأمهرية